# የትግራይ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ
## (2022-006-FB-MR)
## <u>የውሳኔው ማጠቃለያ</u>

የቁጥጥር ቦርዱ ሜታ (Meta) ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ግጭት በተመለከተ ጥቃት ለመፈፀም ያለመ ልጥፍን ለማስወገድ ያስተላለፈውን ውሳኔን እንዲጸና አድርጓል። ይዘቱ የሜታን የግጭት እና ማነሳሳት የማህበረሰብ ደንብን የሚጥስ በመሆኑ መወገዱ ከኩባንያው የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶች ጋር የሚጣጣም ነው። በአጠቃላይ ቦርዱ በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ ሜታ የሰብአዊ መብት ኃላፊነቱን ለመወጣት የበለጠ መስራት እንዳለበት የተገነዘበ ሲሆን ይህንንም ለመፍታት የፖሊሲ ምክረ-ሃሳብ አቅርቧል።

### ስለ ጉዳዩ

ሜታ በፌብሩዋሪ 4፣ 2022 ከኖቬምበር 2020 ጀምሮ በትግራይ እና መንግስት ኃይሎች መካከል የሚደረገዉ ግጭት ተባብሶ በቀጠለበት ወቅት፣ ግጭቱን የሚመመለከት ልጥፍ እንዲመረምር ለቦርዱ ጥያቄ አቀረበ።

ልጥፉ በትግራይ ክልል የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ይፋዊ ገጽ ላይ የወጣ ሲሆን ከ300,000 ጊዜ በላይ ታይቷል። በፌዴራል ሃይሎች የደረሰውን ኪሳራ የሚዳስስ ሲሆን የሀገሪቱ ጦር “ጠመንጃውን” ወደ “አብይ አህመድ ቡድን” እንዲያዞር ያበረታታል። አብይ አህመድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸዉ። ልጥፉ የመንግስት ሃይሎች እጃቸውን እንዲሰጡ እና እምቢ ካሉ እንደሚሞቱም ያሳስባል።

በተጠቃሚዎች ሪፖርት ከተደረገ እና በሜታ አዉቶማቲክ ስርዓት ከተለየ በኋላ፣ ይዘቱ በሁለት አማርኛ ተናጋሪ የይዘት ገምጋሚዎች ማጣሪያ ተደርጎበታል። ሜታም ይዘቱ ፖሊሲዉ የሚጥስ ሆኖ አልተገኘም በማለት ከመድረኩ ሳያስወግደው ቀርቷል።

በጊዜው ሜታ ለኢትዮጵያ የታማኝነት ምርት ማከናወኛዎች ማዕከል (Integrity Product Operations Centre፣ IPOC) በሰራ ላይ አዉሎ ነበር። IPOC ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ የይዘት ግምገማ ለማሻሻል ሜታ የሚጠቀመዉ አሰራር ነዉ። ማዕከሎቹም አገልግሎት የሚሰጡት ለአጭር ጊዜ (ቀናት ወይም ሳምንታት) ሲሆን የሜታን መድረኮች ለመከታተል እና ላልታለመለት ዓለማ ጥቅም ላይ እንዳይዉሉ የሚሰሩ ባለሙያዎችን ያሰባስባሉ። ልጥፉ በIPOC በኩል ለግምገማ ወደ ባለሙያ የተላከ ሲሆን፣ የሜታን የግጭት እና ማነሳሳት ፖሊሲን ስለጣሰ ከሁለት ቀናት በኋላ ተወግዷል።

### ቁልፍ ግኝቶች

ቦርዱ ሜታ ልጥፉን ከፌስቡክ ለማስወገድ በወሰነው ውሳኔ ተስማምቷል።

በኢትዮጵያ ያለው ግጭት ብሄርን ኢላማ ያረገ ጥቃት እና የአለም አቀፍ ህግ ጥሰቶች ተስተዉለውበታል። በዚህ ጽሑፍ ዐዉድ፣ የገጹን ግለ ማህደር እና ተደራሽነት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ልጥፉ ተጨማሪ ግጭት የመፍጠር ዕድሉ ከፍተኛ ነዉ።

በዚህም የተነሳ፣ ቦርዱ «ከፍተኛ ደረጃ ያለው ጥቃት የመፈጸም ሀሳብ ያያዙ ንግግሮችን» የሚከለክለው የሜታ የግጭት እና ማነሳሳት የማህበረሰብ ደንብ በሚጠይቀው መሰረት ልጥፉን ማስወገድ እንደሚያስፈልግ ተስማምቷል። መወገዱም ከሜታ ዕሴቶች ጋር ይጣጣማል፤ የተጠቀሱት ሁኔታዎችም የ«ደህንነት» እና «ክብር» ዕሴቶች ከ«ድምጽ መሆን» ዕሴት በላይ ቅድሚያ እንዲሰጣቸዉ የሚያደርጉ ናቸዉ። ቦርዱ ልጥፉን ማስወገድ ከሜታ የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶች ጋር የሚጣጣም እና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ የሚጣል ምክኒያታዊ ገደብ መሆኑን ቦርዱ ይገነዘባል።

ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሜታ መድረኮቹ የጥላቻ ንግግሮችን ለማሰራጨት እና ገጭትን ለማባባስ ጥቅም ላይ እንደሚዉሉ ያውቃል። በአንዳንድ የግጭት ቀጠናዎች ውስጥ የይዘት ግምገማዉን ለማሻሻል ኩባንያው አዎንታዊ እርምጃዎችን ወስዷል። በአጠቃላይ ቦርዱ ሜታ መድረኮቹ ግጭትን ወይም የአለም አቀፍ ህግ ጥሰቶች እንዲፈፀሙ ለማነሳሳት ጥቅም ላይ የመዋላቸዉን ስጋት ለመቀነስ፣ በግጭት ቀጠናዎች ውስጥ ይዘትን የሚገመግምበት መርህን የተከተለ ግልጽ ስርዓት የመዘርጋት የሰብአዊ መብት ኃላፊነት እንዳለበት ተገንዝቧል። ይህንን ኃላፊነት ለመወጣትም የበለጠ መሥራት አለበት።

ለምሳሌ፣ ሜታ በትጥቅ ግጭት ሁኔታዎች ውስጥ የግጭት እና ማነሳሳት ፖሊሲውን እንዴት እንደሚተገብር፣ ምን ዓይነት በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ፖሊሲዎች እንዳሉ ወይም እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በተመለከተ በቂ መረጃ አይሰጥም። አሁን ያለው አካሄድ በግጭት አካባቢዎች ውስጥ የይዘት ግምገማዉ ወጥነት እንደሚጎድለው ያሳያል፣ ታዛቢዎች ኩባንያው የሩስያ ዩክሬንን ግጭት ከሌሎች በተለየ መልኩ ያስተናግዳል ሲሉ ይወቅሳሉ።

ሜታ የስራ ወጪዎቹን ድልድል የሚመራበትን «ለአደጋ የተጋለጡ ሀገሮች» መዝገብ አዘጋጅቻለው ብሏል። ነገር ግን ለቦርዱ የዚህን ሂደት ፍትሃዊነት ወይም ውጤታማነት ለመገምገም የሚያችል በቂ መረጃ አልሰጠም። በዚህ ጉዳይ የተመደበው IPOC ይዘቱ እንዲወገድ አድርጓል። ይሁን እንጂ፣ ይዘቱ ለሁለት ቀናት መድረኩ ላይ ቆይቷል። ይህ የሚያመለክተው «ለአደጋ የተጋለጡ ሀገሮች» የሚባለው ስርዓት እና IPOC የግጭት ሁኔታዎችን ለመቋቋም በቂ አንዳልሆኑ ነው። በሜታ አሰራር መሰረት፣ IPOC «ለዓመታት የዘለቀን ግጭት ለመፍታት ዘላቂ መፍትሄ እንዲሆኑ የታሰቡ አይደሉም»። ቦርዱ ሜታ ዘለቄታዊ መፍትሄ ለመገንባት ተጨማሪ ወጪ ማድረግ እንደሚያስፈልገው ተገንዝቧል።

## የቁጥጥር ቦርዱ ውሳኔ

የቁጥጥር ቦርዱ ሜታ ልጥፉን ለማስወገድ የሰጠውን ውሳኔ ይደግፋል።

በተጨማሪም ቦርዱ የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች ያቀርባል፡-

- ሜታ በግልጽነት ማዕከል ውስጥ የቀውስ ፖሊሲ ፕሮቶኮሉ በተመለከት መረጃ ማሳተም አለበት።
- ሜታ ለግጭት ጊዜ የሚሆን ይዘትን በብቃት ለመገምገም እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልገውን እውቀት፣ አቅም እና ቅንጅት የሚያቀርብ ዘላቂ የውስጥ አሰራር የመመስረት አዋጭነትን መገምገም አለበት።

*የዉሳኔ ማጠቃለያ የጉዳዩን አጠቃላይ እይታ የሚሰጥ እንጂ አስገዳጅ ወይም አሳሪ አይደለም።

## ዝርዝር ውሳኔ

### 1. የውሳኔ ማጠቃለያ

የቁጥጥር ቦርዱ ሜታ የግጭት እና ማነሳሳት የማህበረሰብ ደንብን በመጣሱ ይዘቱን ከፌስቡክ ለማስወገድ የሰጠውን ውሳኔ ይደግፋል። ቦርዱ በዚህ ዉሳኔ ላይ የተለመከተዉን ይዘት ማስወገዱ በትጥቅ ግጭት ጊዜ ሜታ ካለብት የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ተገንዝቧል። እንዲሁም ቦርዱ ሜታ መድረኮቹ ግጭትን ለመቀስቀስ ወይም የአለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰትን ለመፈጸም ጥቅም ላይ የመዋላቸውን ስጋት ለመቀነስ፣ በግጭት አካባቢዎች ውስጥ ይዘትን የሚገመግምበት መርህን የተከተለ ግልጽ የሆነ ስርዓት የመዘርጋት የሰብአዊ መብት ኃላፊነት እንዳለበት ተገንዝቧል። ቦርዱ ሜታ የሰብአዊ መብት ሃላፊነት ጋር ያሚጣጣሙ ሁሉንም እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን በድጋሚ ያስገነዝባል።

### 2. የጉዳዩ ማብራሪያ እና የጀርባ ምስል

በፌብሩዋሪ 4፣ 2022፣ ሜታ ኖቬምበር 5 ቀን 2021 በፌስቡክ ላይ የተለጠፈ ይዘትን በሚመለከት ቦርዱ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጥያቄ አቀረበ። ይዘቱ የተለጠፈው የትግራይ ክልል ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ (Tigray Communication Affairs Bureau) ይፋዊ ገጽ መሆኑን በሚገልጽ፣ የትግራይ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ገፅ ላይ ነው። ይዘቱ የተለጠፈው በፌዴራል መንግሥቱ ይፋዊ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው። የትግራይ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የትግራይ ክልል መንግስት አካል ነው። ከኖቬምበር 2020 ጀምሮ፣ ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ («ፌዴራል መንግስት») የትጥቅ ግጭት ውስጥ ገብተዋል። ህወሓት የትግራይ ገዥ ፓርቲ ሲሆን የትግራይ መከላከያ ሰራዊት ደግሞ የህወሓት የታጠቀ ክንፍ ነው።

ልጥፉ በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የሚመራው የፌደራል ሀገር መከላከያ ሰራዊት ከህወሀት ጋር ባደረገው የትጥቅ ግጭት የደረሰበትን ኪሳራ ይዳስሳል። ልጥፉ የሀገሪቱ ጦር «ጠመንጃውን ወደ ፋሽስቱ አቢይ አህመድ ቡድን በማዞር የጎዳውን ህዝብ እንዲክስ» ያበረታታል። በመቀጠልም የታጠቁ ሃይሎች ህይወታቸውን ለማዳን ተስፋ ካደረጉ ለህወሓት እጅ እንዲሰጡ እንዲህ ሲል ያሳስባል«እምቢተኛ ከሆኑ፣ የታጠቁ ኃይሎች የመጨረሻ እጣ ፈንታ ሞት መሆኑን ሁሉም ሰው ማወቅ አለበት»።

በፌደራል መንግስት እና በህወሓት መካከል ያለው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው የፌደራል መንግስቱ በ2020 የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን በመጥቀስ ምርጫው ለሌላ ጊዜ ባራዘመ ጊዜ ነው። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ወረርሽኙን እንደ ሰበብ ተጠቅመዋል ሲሉ ከሰዋል። የፌደራል መንግስት ምርጫ እንደማይደረግ መግለጫ ቢሰጥም፣ የትግራይ ክልል መንግስት በክልሉ ውስጥ ምርጫ በማካሄድ ህወሓት በከፍተኛ ድምፅ አሸንፏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በትግራይ የፌደራል ወታደራዊ ካምፕ ላይ ለደረሰው ጥቃት ምላሽ በኖቬምበር 2020 በትግራይ ሃይሎች ላይ ወታደራዊ ዘመቻን አውጇል። የፌደራል ሃይሎች የትግራይን ዋና ከተማ መቀሌ ተቆጣጥረው ነበር። ከስምንት ወራት ጦርነት በኋላ፣ የፌደራል ሃይሎች እና አጋሮቻቸው ከመቀሌ ለቀው ሲወጡ ህወሓትም ከተማዋን መልሶ ተቆጣጠረ። በሜይ 2021፣ የፌደራል መንግስት ህወሓትን በአሸባሪነት ፈረጀው።

በኖቬምበር 2፣ 2021፣ ይዘቱ ከመለጠፉ ቀናት በፊት፣ ህወሀት ከትግራይ አልፎ የአማራ እና አፋር ክልል የተወሰኑ ቦታዎችን ከተቆጣጠረ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቷል። እንዲሁም የፌደራል መንግስት ህወሀት ወደ ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ እየተቃረበ በመሆኑ ዜጎች መሳሪያ እንዲያነሱ ጥሪ አቅርቧል። ኖቬምበር 5 ይዘቱ በተለጠፈበት ቀን ህወሃትን ጨምሮ፣ ዘጠኝ ተቃዋሚዎች በፌደራል መንግስቱ ላይ ጫና ለመፍጠር እና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ከስልጣን ለማውረድ ህብረት ፈጥረዋል።

የትግራይ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ገጽ ወደ 260,000 ተከታዮች ያሉት ይፋዊ ገጽ ነው፣ ማለትም በማንኛውም የፌስቡክ ተጠቃሚ ሊታይ ይችላል። ገፁ ወይም ግለ ማህደሩ የአንድ ሰው ወይም አካል ትክክለኛ መገኛ መሆኑን በሚያረጋግጥ ሰማያዊ ምልክት ባጅ የተረጋገጠ ነው። ይዘቱ ከ300,000 ጊዜ በላይ ታይቷል፣ ከ1,000 ያነሰ ጊዜ ደግሞ ተጋርቷል።

ከኖቬምበር 5 ጀምሮ፣ ይዘቱ የግጭት እና ማነሳሳት፣ የአደገኛ ግለሰቦች እና ድርጅቶች እና የጥላቻ ንግግር ፖሊሲዎችን በመጣሱ፣ በ10 ተጠቃሚዎች ሪፖርት ተደርጓል። በተጨማሪም፣ የሜታ አዉቶማቲክ ስርዓት፣ ይዘቱ ጥሰት ፈጽሞ ሊሆን ይችላል በሚል ወደ ተጨማሪ ግምገማ ልኮታል። የሁለት አማሪኛ ተናጋሪ ገምጋሚዎችን ግምገማ ተከትሎ፣ ሜታ ይዘቱ ፖሊሲዎቹን እንደማይጥስ እና ከመድረክ ላይ እንደማያስወግደው ወስኗል።

ኖቬምብር 4፣ ይዘቱ ከመለጠፉ ከአንድ ቀን በፊት፣ ሜታ በኢትዮጵያ በፍጥነት እየተከሰተ ያለውን ሁኔታ ለመከታተል እና በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት የታማኝነት ምርት ማከናወኛ ማዕከልን (IPOC) እንዲቋቋም አደረገ። በሜታ አሰራር መሰረት፣ IPOC የሜታ መድረኮች ላልተገባ ዓላም ጥቅም ላይ እንዳይዉሉ ለመከታተል በኩባንያው ውስጥ ለአጭር ጊዜ የሚሰበሰቡ የዘርፍ ባለሙያዎች ቡድን ነው። በIPOC በኩል፣ ይዘቱ ተጨማሪ ግምገማ ይደረግበት ዘንድ ወደ ፖሊሲ እና የዘርፉ ባለሙያዎች ተመርቷል። ይሄን ግምገማ ተከትሎ፣ ሜታ ይዘቱ «ከፍተኛ ደረጃ ያለው ጥቃት የመፈጸም ሀሳብ ያያዙ ንግግሮችን»ን የሚከለክለውን፣ የግጭት እና ማነሳሳት ፖሊሲን የሚጥስ መሆኑን ወስኗል። ይዘቱ ከመወገዱ በፊት ለሁለት ቀናት ያህል መድረኩ ላይ ቆይቷል።

ግጭቱ ከጀመረበት ኖቬምበር 2020 ጀምሮ፣ በግጭቱ ውስጥ ባሉ በሁሉም አካላት የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ህግ ጥሰቶችን መፈፀማቸውን የሚያሳዩ አስተማማኝ ሪፖርቶች ነበሩ። በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት በጋራ በተደረገ [የምርመራ ሪፖርት ]ማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፣ ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ፣ በሰላማዊ ዜጎች እና በቁጥጥር ስር የዋሉ ወታደሮች ያለፍርድ መግደል፣ አፈና፣ በግዳጅ መሰወር እና ጾታዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ ከሌሎች አለም አቀፍ ወንጀሎች መካከል መኖራቸውን አመላክቷል (በተጨማሪ [የኢትዮጵያ የሰላም ታዛቢን ይመልከቱ])። የጋራ የምርመራ ቡድኑ በግጭቱ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸው ሰዎች በግጭቱ ውስጥ በተሳተፉ ሁለቱም ወገኖች መገደላቸውን አረጋግጧል። ይህም ብሄርን ኢላማ ያደረጉ እና የበቀል ግድያዎችን ይጨምራል። የፌደራል ኃይሎችም ሆኑ የትግራይ ኃይሎች «በትግራይ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች፣ በወታደራዊ ካምፖች፣ በእስር ቤቶች፣ በተጎጂዎች መኖሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም ሚስጥራዊ እና የማይታወቁ ቦታዎችን ጨምሮ በሰላማዊ ሰዎች እና ምርኮኛ ተዋጊዎች ላይ ማሰቃየትን እና እንግልትን ፈጽመዋል»። ከህወሀት ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ ግለሰቦች በኃይል እንዲጠፉ ተደርገዋል ወይም በዘፈቀደ ታስረዋል፣ ሚስቶቻቸዉም በፌደራል ታጣቂ ሃይሎች ጾታዊ ጥቃት ደርሰባቸዋል። በተመሳሳይ፣ የፌደራል የመከላከያ ሰራዊት አባላት ሚስቶች በትግራይ ታጣቂዎች ጾታዊ ጥቃት ደርሰባቸዋል ወይም ተደፍረዋል። ብዙ ሰዎች በቡድን ተደፍረዋል። የፌደራል ታጣቂ ሃይሎች ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ሰብአዊ እርዳታ እንዲገባ ለማመቻቸት ፍቃደኛ አልነበሩም። ሌሎች የታጠቁ ቡድኖች እና ሚሊሻዎችም በዚህ ድርጊት ላይ ተሳትፈዋል። ኤርትራ በግጭቱ ውስጥ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጦር ደግፋለች። ምንም እንኳን የጋራ ምርመራው ከኖቬምበር 3፣ 2020 እስከ ጁን 28፣ 2021 ድረስ የተከሰቱትን ክስተቶች ቢሸፍንም፣ ግኝቶቹ ለዚህ ዉሳኔ ጠቃሚ ግብዓት የሰጡ ሲሆን፣ በኖቬምበር 2021 በኋላ ህወሀት ከትግራይ ውጭ ያሉ ግዛቶችን በሚቆጣጠርበት ጊዜ ለተፈጠረዉ የግጭት መባባስ ጠቃሚ አውድ አቅርበዋል።

### 3. የቁጥጥር ቦርድ ስልጣን እና ወሰን

ቦርዱ ሜታ ለግምገማ የሚጠቀምባቸውን ውሳኔዎች የመገምገም ስልጣን አለው (ቻርተር አንቀጽ 2፣ ክፍል 1፣ በህጎች አንቀጽ 2፣ ክፍል 2.1.1) ። ቦርዱ የሜታን ውሳኔ ሊያጸና ወይም ሊሽር ይችላል (ቻርተር አንቀጽ 3፣ ክፍል 5) ውሳኔው በኩባንያው ላይ አስገዳጅ ነው (ቻርተር አንቀጽ 4)። በተጨማሪም ሜታ ይህንን ውሳኔ በተመሳሳይ አውድ እና ይዘት ላይ እንዴት ተግባራዊ ሊገረግ እንደሚችል መመርመር አለበት (ቻርተር አንቀጽ 4)። የቦርዱ ውሳኔዎች ሜታ ምላሽ ሊሰጥባቸው የሚገቡ አስገዳጅ ያልሆኑ የፖሊሲ ምክረ-ሃሳቦችን ሊያካትቱ ይችላሉ። (ቻርተር አንቀጽ 3፣ ክፍል 4፣ አንቀጽ 4)።

### 4. የስልጣን ምንጭ

የቁጥጥር ቦርዱ የሚከተሉትን ለውሳኔው ግብዓት ተጠቅሟል፡-

## I. *የቁጥጥር ቦርድ ውሳኔዎች፡-*

ጠቃሚ የሆኑ የቀድሞ የቁጥጥር ቦርድ ውሳኔዎች የሚከተሉትን ናቸው፡-

- «በራያ ቆቦ ተፈጽመዋል የሚባሉ ወንጀሎች» [ውሳኔ 2021-014-FB-UA]፡- ቦርዱ የፌስቡክ የማህበረሰብ ደንቦች ያልተረጋገጡ ወሬዎች በጦርነት እና ግጭት ውስጥ በሰዎች ህይወት እና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ስጋት እንደሚፈጥሩ ማንጸባረቅ እንዳለባቸው መክሯል። ቦርዱ የሜታ መድረኮች በኢትዮጵያ ያለውን የግጭት አደጋ ከፍ ለማድረግ እንዴት ጥቅም እንደዋሉ ገለልተኛ የሰብአዊ መብት ጥናት ማስጠናት እንዳለበት ምክረ-ሃሳብ አቅርቧል።
- «የቀድሞው የፕሬዚዳንት ትራምፕ እገዳ» [ውሳኔ 2021-001-FB-FBR]፡- ቦርዱ ሜታ ስለ ቀውስ ሁኔታዎች ፖሊሲ አዘጋጅቶ ማሳተም እንዳለበት ምክረ ሃሳብ ሰጦቷል። ቦርዱ ወደፊት በሚመለከታቸው አካላት ሊደረጉ ስለሚችሉ ከፍተኛ የአለም አቀፍ የወንጀል፣ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊ ህግ ጥሰቶችን ምርመራ አና ክስ ይረዳ ዘንድ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማቆየት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማጋራት አስፈላጊ መሆኑን መክሯል።
- «የሱዳን ሰቅጣጭ ቪዲዮ ዉሳኔ» [ውሳኔ 2022-002-FB-MR]፡- ቦርዱ «የቀድሞው የፕሬዚዳንት ትራምፕ እገዳ» ዉሳኔ ላይ እንደገለፀው ሜታ «መደበኛ የሥራ ሂደቶቹ ጉዳቶችን የማይከላከሉ ሁኔታ ሲፈጠር» ተግባራዊ የሚደረጉ የቀውስ ሁኔታዎችን የሚመለከት ፖሊሲ እንዲያዘጋጅ እና እንዲያሳትም ያቀረበውን ሃሳብን በድጋሚ ያሳስባል።

## II. *የሜታ የይዘት ፖሊሲዎች፡-*

*የፌስቡክ የማህበረሰብ ደንቦች፡-*

ሜታ በግጭት እና ማነሳሳት ፖሊሲው ስር «ከባድ ጥቃትን የሚያነሳሳ ወይም የሚያመቻች» ማንኛውንም ይዘት እንደሚያስወግድ ገልጿል። ፖሊሲው በሰዎች እና አከባቢዎች ያነጣጠሩ «ለሞት ሊዳርጉ የሚችሉ እና (ሌሎች ከፍተኛ ጉዳት ያላቸው ጥቃቶችን) ዛቻዎችን ይከለክላል»። እንዲሁም «ከፍተኛ ደረጃ ያለው ጥቃት የመፈጸም ሀሳብ ያያዙ ንግግሮችን ይከለክላል»።

## III. *የሜታ ዕሴቶች፡-*

የሜታ ዕሴቶች በፌስቡክ የማህበረሰብ ደንቦች መግቢያ ላይ ተዘርዝረዋል። የ«ድምጽ መሆን» ዕሴት «ቅድሚያ» የሚሰጠው በመሆን ተገልጿል፡-

*የማህበረሰብ ደንቦቻችን ግብ ሁሌም ሀሳብን መግለጫ ቦታ መፍጠር እና ለሰዎች ድምጽ መስጠት ነው። [እኛ የምንፈልገው] ምንም እንኳን አንዳንዶች ላይስማሙባቸው ወይም ሊቃወሟቸው ቢችሉም፣ ሰዎች ለነሱ አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ላይ በግልጽ እንዲናገሩ ነዉ።*

ሜታ ለሌላ አራት ዕሴቶች ሲባል «ድምጽ መሆን»ን ዕሴት ሊገድብ ይችላል፣ ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ እዚህ ጠቃሚ ናቸው፡

«ደህንነት»፡- *በሰዎች አካላዊ ደህንነት ላይ ጉዳትን ሊያስከትል የሚችል ይዘትን እናስወግዳለን።*

*«ክብር»፡- ሰዎች የሌሎችን ክብር እንዲያከብሩ እንጠብቃለን እንጂ ሌሎችን እንዲያጠቁ ወይም እንዲያሳንሱ አንፈቅድም።*

### *IV. የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ህጎች*

በ2011 በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት የፀደቀው የተባበሩት መንግስታት የንግድ እና የሰብአዊ መብቶች መመሪያ (UNGPs)፣ ለግል ንግድ ተቋማት የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶች በፈቃደኝነት የሚሳተፉበት ማዕቀፍ አቋቁመዋል። በ2021፣ ሜታ የኩባንያውን ሰብአዊ መብቶች ፖሊሲውን አስታውቋል፣ በዚህም በUNGPs መሠረት ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ያልዉን ቁርጠኝነት ድጋሚ አረጋግጧል። በተልየ መልኩ፣ UNGP በግጭት ሁኔታ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የንግድ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ኃላፊነት ይጥላል («የንግድ ተቋማት፣ ሰብአዊ መብቶች እና በግጭት የተጎዱ ቀጠናዎች፡- ወደ ከፍተኛ እርምጃ» A/75/212)። ቦርዱ በዚህ ዉሳኔ ላይ የሜታ የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶችን በተመለከተ የሰጠው ትንታኔ በሚከተሉት የሰብአዊ መብት ህጎችን ያገናዘበ ነዉ።

- ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፡- *አንቀጽ 19፣ በዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን (ICCPR)፣ በአጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 34፣ በሰብአዊ መብት ኮሚቴ፣ 2011፤ በተባበሩት መንግስታት የአመለካከት እና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ልዩ ዘጋቢ፣ እንደዘገበው፡* A/HRC/38/35 (2018) እና A/73/348 (2018)።

- በህይወት የመኖር መብት፡- አንቀጽ 6፣ ICCPR፣ አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 36፣ የሰብአዊ መብት ኮሚቴ (2018)።

- ከስቃይ ወይም በጭካኔ የተሞላ፣ ኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ ቅጣት የመጠበቅ መብት፡- አንቀጽ 7፣ ICCPR።

- ደህንነት የማግኘት መብት፡- አንቀጽ 9፣ አንቀጽ 1፣ ICCPR።

## 5. የተጠቃሚዉ አስተያየት

ሜታ ጉዳዩን ወደ ቦርዱ መምራቱን እና ቦርዱም ጉዳዩን ተቀብሎ ለመመርመር መወሰኑን ተከትሎ፣ ተጠቃሚው ይህንን የቦርዱን ዉሳኔ የሚያሳውቅ መልእክት ተልኮላቸዋል። ተጠቃሚዉ ለቦርዱ

አስተያየት እንዲያቀርቡ እድል ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን ተጠቃሚው ምንም አስተያየት አላቀረቡም።

## 6. የሜታ ገለፃዎች

ሜታ ጉዳዩን ወደ ቦርዱ ሲያቀርብ ይዘቱ «ለዜና ብቁ ሊሆን የሚችል ይፋዊ የመንግስት ንግግር» ነገር ግን እየተካሄደ ባለ ግጭት ውስጥ ጥቃትን ሊቀሰቅስ የሚችል ይዘት በመሆኑ፣ ይዘቱን በሚመለከት የሚሰጠዉን ዉሳኔ ከባድ ያደርገዋል ሲል ገልጿል። ሜታ የዜና ብቁነት ፈቃድ ለአካላዊ ጥቃት ወይም ጉዳት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ለሚችል ይዘት ላይ የሚሰጥ ባለመሆኑ ምክንያት ፈቃዱን አለመስጠቱን ገልጿል።

ከ2020 መገባደጃ ጀምሮ፣ ሜታ ኢትዮጵያን ደረጃ አንድ በአደጋ ላይ የምትገኝ፣ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ ያለች ሀገር አድርጎ እንደሚወስዳት ገልጿል። በሜታ አሰራር መሰረት፣ ሀገራትን በአደጋ ላይ የሚገኙ ብሎ መመደብ በረጀም ጊዜ የመድረኩን ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር ለሚያፈሰው መዋእለ-ንዋይ ቅድምያ ሰጥቶ ለመስራት የሚከተለው አካሄድ አካል ነው። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ ካለው ከፍተኛ ስጋት ጋር በተያያዘ ሜታ ኢትዮጵያ ውስጥ በተናጋሪ ብዛት ቀዳሚ በሆኑት አማርኛ እና አፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች የይዘት መለያዎችን (በአዉቶማቲክ የማህበረሰብ ደረጃን ሊጥሱ የሚችሉ ይዘቶችን ማጣሪያ መንገድ) አዘጋጅቷል ። ኩባንያው እንደገለጸው፣ የመጀመሪያዎቹ የአማርኛ እና አፋን ኦሮሞ መለያዎች ወደ ስራ የገቡት በኦክቶበር 2020 ነዉ። ጁን 2021፣ ሜታ በአማርኛ እና አፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች የ «ፀብ-አጫሪ ንግግር» መለያዎችን ሥራ አስጀምሯል (የጥላቻ ንግግር፣ የግጭት እና ማነሳሳት፣ እንዲሁም የጉልቤነት እና ትንኮሳ ፖሊሲዎች የሚመለከት ይዘትን እንዲለዩ ተደርገው የተሰናዱ የማሽን ትምህርት መሳሪያዎች)። ኩባንያው ለተባባሰው ግጭት ምላሽ ለመስጠት ኖቬምበር 4፣ 2021 IPOC ለኢትዮጵያ አቋቋመ። IPOC በተለምዶ ለብዙ ቀናት ወይም ሳምንታት ይሰራሉ። IPOC የሚሰበሰበው፣ አስቀድመዉ ለታቀዱ ክንውኖች (ለምሳሌ ምርጫ) እና ለአደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ላልታሰቡ ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት ነው። ማንኛውም የሜታ ሰራተኛ IPOC እንዲቋቋም ሊጠይቅ ይችላል። ጥያቄው በርካታ ደረጃዎች ባሉት የኩባንያው የስራ ፣ ፖሊሲ እና የምርት ቡድንን ጨምሮ፣ በበርካታ ባለድርሻ አካላት ይገመገማል። IPOC የተለያየ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፣ በመድረክ ላይ ያለውን ይዘት በመከታተል ከፍ ያለ የማስተባበር እና የግንኙነት ስራዎችን ይሰራል። በኖቬምበር 2021 ለኢትዮጵያ የተቋቋመዉ IPOC ደረጃ ሶስት ነበር፣ ይህም «በሜታ ውስጥ ትልቁን የማስተባበር እና የግንኙነት ስራን ለመስራት ያስችላል»። ሜታ እንደገለጸው፣ IPOC "የአጭር ጊዜ መፍትሄ" ነዉ። ይህም «ብዙ ጉዳዮችን በቀውስ ወይም በከፍተኛ አደጋ ሁኔታ ውስጥ እንዴት መፍታት እንደሚቻል የሚያገለግሉ ናቸው። ለዓመታት ለዘለቁ ግጭቶች ዘላቂ እና የረጅም ጊዜ መፍትሄ እንዲሆን የታሰበ አይደለም»።

«በራያ ቆቦ ውስጥ ተፈጽመዋል የሚባሉት ወንጀሎች» ዉሳኔን ላይ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን መጠበቅ እና የብሄር ግጭት ስጋት መቀነስ መካከል ያለውን ውጥረት ለማስታረቅ የግጭቱን ዝርዝር ሁኔታ በጥንቃቄ መመልከት ይጠይቃል የሚለውን ሀሳብ የቦርዱን ትንታኔ ሜታ

እንደ ማጣቀሻ ተጠቅሟል። ሜታ የጭካኔ ወንጀሎች በሁሉም የግጭቱ አካላት መፈጸማቸውን የሚገልጹ ማስረጃዎችን ተመልክቷል። ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ወደፊት ሊፈጸም ስሚችል ግጭት ማስጠንቀቂያ የመስጠት ጠቀሜታ ቢኖረውም፣ ሜታ ለቦርዱ እንደገለጸው ከስጋቱ አይነት በመነሳት፣ ተናጋሪው ያለው ተደማጭነት እና ይዘቱ በተለጠፈበት ወቅት በኢትዮጵያ በፍጥነት እየተባባሰ ከመጣው ሁኔታ ጋር ተያይዞ፣ የ«ደህንነት» ዕሴት ዋጋ ከሌሎች ዕሴቶች የበለጠ በመሆኑ ይዘቱን ማስወገድ መድረክ ላይ እንዲቀር ከማድረግ ይሻላል።

ቦርዱ ሜታን 20 ጥያቄዎች ጠይቋል። ሜታ 14 ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ እና ስድስት ጥያቄዎችን በከፊል መልሷል። በከፊል ምላሽ የሰጠባቸዉ ጉዳዮች ኩባንያው በትጥቅ ግጭት ሁኔታዎች ውስጥ የይዘት ግምገማዉን የሚካያካሄድበት መንግድ፣ የይዘት ፖሊሲዎችን በመጣስ ምክንያት በተጠቃሚዎች ላይ የሚጣል ገደብ እና ተጨማሪ የማጣራት ሂደት ጋር የተያያዘ ነው።

## 7. የህዝብ አስተያየቶች

የቁጥጥር ቦርዱ ከዚህ ዉሳኔ ጋር የተያያዙ ሰባት የህዝብ አስተያየቶችን ተቀብሎ ተመልክቷል። ከአስተያየቶቹ ውስጥ አንዱ ከእስያ ፓሲፊክ እና ኦሺኒያ፣ ሶስቱ ከአውሮፓ፣ አንዱ ከሰሃራ በታች ካሉ አፍሪካ ሀግራት እና ሁለቱ ደግሞ ከአሜሪካ እና ካናዳ ቀርቧል።

የቀረቡት አስተያየቶች የሚከተሉትን ጭብጦች ያካትታሉ፡ በተለያዩ የትጥቅ ግጭቶች ውስጥ የሜታ አሰራር ወጥ አለመሆን፣ በትጥቅ ግጭት ወቅት የተፋላሚዎች የጥቃት ዛቻዎች የሚያስከትሉት አደጋ፣ ሜታ በኢትዮጵያ የሚያካሄደው የይዘት ግምገማ ችግሮች እና የማህበራዊ ሚዲያ የፕሬስ ነፃነት በሌለባቸው አካባቢዎች ውስጥ ያለው ሚና፣ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እና በፌስቡክ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚሰነዘረው የጥላቻ ንግግር ግጭትን በማስፋፋት ረገድ ያለው ሚና፣ በኢትዮጵያ ስላለው ግጭት ትክክለኛ ዳራ እና በትጥቅ ግጭት ወቅት የሚደረግ ንግግርን ለመቆጣጠር የሚቀረፁ ፖሊሲዎችን የትጥቅ ግጭት ህጎችን ከግምት ውስጥ የማስገባትን አስፈላጊነትን ያካትታል።

ለዚህ ዉሳኔ ግብዓት የቀረቡ የህዝብ አስተያየቶችን ለማንበብ፣ እባክዎ ይህንን ማስፈጠሪያ ይጫኑ።

በኤፕሪል 2022፣ ቀጣይነት ያለው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የማረጋገጥ ሂደት ቦርዱ መሠረት የትጥቅ ግጭቶችን በሚመለከት የይዘት ግምገማን በተመለከተ የመብት ተሟጋች ድርጅቶች ተወካዮችን፣ ምሁራንን፣ መንግሥታዊ ድርጅቶችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን አማክሯል። ውይይቶቹ በግጭት ውስጥ ባሉ ወገኖች የንግግር አያያዝ እና የግጭት ሁኔታዎች ውስጥ የጥቃት እና ማነሳሳት ፖሊሲን ተግባራዊ የሚደረግበትን መንገድ ያጠቃልላል።

## 8. የቁጥጥር ቦርድ ትንተኔ

በርዱ ይህ ይዘት ወደነበረበት መመለስ አለበት ወይ የሚለውን ጉዳይ እና አጠቃላይ ለሜታ የይዘት ግምገማ ሥራ ያለውን እንድምታ በሶስት መንገዶች መዝኗል። እነዚህም፡- የሜታ የይዘት ፖሊሲዎች፣ የኩባንያው ዕሴቶች እና የሰብአዊ መብቶች ኃላፊነቶች ናቸው።

## 8.1 ከሜታ የይዘት ፖሊሲ ጋር መጣጣም

በርዱ ይዘቱን ከመድረክ ላይ ማስወገድ ከግጭት እና ማነሳሳት የማህበረሰብ ደንብ ጋር የሚስማማ መሆኑን ተገንዝቧል። ፖሊሲው በሰዎች እና አከባቢዎች ላይ ያነጣጠሩ «ለሞት ሊዳርጉ የሚችሉ እና (ሌሎች ከፍተኛ ጉዳት ያላቸው የጥቃት) ዛቻዎችን ይከለክላል»። በርዱ ይዘቱ ቀድሞውንም ከፍተኛ ጉዳት ባስከተለ የትጥቅ ግጭት ውስጥ ተጨማሪ ጥቃት ሊቀሰቅስ ወይም ሊያበረታታ የሚችል ጥሪ ተብሎ በምክንያታዊነት ሊተረጎም ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። ስለዚህ፣ ይዘቱ «ከፍተኛ ደረጃ ያለው ጥቃት የመፈጸም ፍላጎት ያያዙ ንግግሮች» የሚለውን የሜታ ክልከላ ይጥሳል።

## 8.2 የሜታ ዕሴቶችን ማክበር

በርዱ ይህንን ይዘት ከመድረክ ላይ ማስወገድ ከሜታ የ«ደህንነት» እና «ክብር» ዕሴቶች ጋር የሚስማማ ነው ሲል ደምድሟል።

በርዱ የፕሬስ እና የዜጎች ነፃነት ታሪክ ዝቅተኛ በሆነበት እና የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ስለ ትጥቅ ግጭት መረጃን ለማስተላለፍ ቁልፍ ሚና በሚጫወቱበት ሀገር ዉስጥ የ«ድምጽ መሆን» ዕሴት አስፈላጊነትን ይገነዘባል። ነገር ግን በትጥቅ፣ በብሄር ግጭት ታሪክ እና በአለም አቀፍ ህግ ጥሰት አውድ ውስጥ ተጠቃሚዎችን ከፍተኛ አድጋ ከሚፈጥር ይዘቶች ለመጠበቅ የ«ደህንነት» እና «ክብር» ዕሴቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል። በዚህ ዉሳኔ ላይ የተመለከተዉ ይዘት «የአብይ አህመድን ቡድን» ለመግደል የቀርበ ጥሪ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ከዚህም በላይ ለህወሃት እጅ በማይሰጡት ላይ የተቃጣ ዛቻ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፣ በመሆኑም በኢትዮጵያ የፌዴራል ኃይሎች እና የፖለቲካ መሪዎች ህይወት እና አካላዊ ደህንነት ላይ አደጋ ይፈጥራል። ይዘቱ በክልል አስተዳደር አካል የተጋራ ቢሆንም፣ የጉዳት አደጋን ከመቀነስ በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጠንካራ የህዝብ ጥቅም ሊያጠብቅ የሚችል መረጃ አልያዘም።

## 8.3 ከሜታ የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶች ጋር መስማማት

በርዱ በዚህ ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ይዘት ማስወገዱ ከሜታ የሰብአዊ መብት ኃላፊነቶች ጋር የሚስማማ መሆኑን ተገንዝቧል። በትጥቅ ግጭት ወቅት፣ ኩባንያው ይዘቱ ግጭትን ሊቀሰቅስ የሚችልበት ምክንያታዊ እድል በሚኖርበት ጊዜ፣ ይዘትን ለመገምገም መርህን የተከተለ እና ግልጽነት ያለው የይዘት ቁጥጥር ስርዓት የመዘርጋት ሃላፊነት አለበት። በርዱ ይዘት በትጥቅ ግጭት ወቅት በቀጥታ ለጉዳት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍ ማለቱን ይረዳል። በርዱ በአሁኑ ወቅት ሜታ

በግጭት ቀጠናዎች ውስጥ ያለውን የይዘት ግምገማ መርህ ላይ ያተኮረ እና ግልጽነት ያለው መዋቅር እንደሌለው ተገንዝቧል።

*ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት (አንቀጽ 19 ICCPR)*

የICCPR አንቀጽ 19፣ ስለ ግጭት መረጃ የመፈለግ እና የመቀበል መብትን ጨምሮ፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን በተመለከተ ሰፊ ጥበቃን ይሰጣል። ነገር ግን፣ መብቱ በተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ሊገደብ ይችላል፣ እነዚህም የሰስት ክፍል ህጋዊነት (ግልጽነት) ቅቡልነት፣ አስፈላጊነትን እና ተመጣጣኝነት ምዘናን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ሜታ በUNGP ስር ያሉ ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር እና የትጥቅ ግጭት ሁኔታዎችን ጨምሮ የይዘት ውሳኔዎቹ እንደ ICCPR ያሉ ህጎችን ለማመሳከር ቁርጠኝነቱን ገልጧል። የራባት የድርጊት መርሃ ግብርም በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቃሚ መመሪያ ይሰጣል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሐሳብ ነፃነት ልዩ ዘጋቢ እንዳስታወቀው፣ ምንም እንኳን «ኩባንያዎች ከመንግስታ አንድ አይነት ግዴታዎች ባይኖርባቸውም፣ ያላቸው ተፅእኖ የተጠቃሚዎቻቸውን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ከመጠበቅ አንጻር ተመሳሳይ ጥያቄዎችን እንዲገመግሙ ያደርጋቸዋል»(A/74/486፣ አንቀጽ 41)።

*I. ህጋዊነት (የህጎቹ ግልጽነት እና ተደራሽነት)*

ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ የተጣለ የትኛውም ገደብ በመድረኩ ላይ ምን አይነት ይዘት እንደሚፈቀድ እና እንደማይፈቀድ ለተጠቃሚዎች እና የይዘት ገምጋሚዎች መመሪያ ለመስጠት በሚያስችል አኳሃን ተደራሽ እና ግልጽ መሆን አለበት። ግልጽነት ወይም ትክክለኛነት የማይኖር ከሆነ ወጥ ወዳልሆነ እና የዘፈቀደ የህጎቹ አፈፃፀም ሊያመራ ይችላል።

የግጭት እና ማነሳሳት ፖሊሲው «ለሞት ሊዳርጉ የሚችሉ ዛቻዎችን» እና በተለይም «ከፍተኛ ጥቃትን የመፈጸም ሃሳብ የያዙ ንግግሮችን» ይከለክላል። ቦርዱ በዚህ ዉሳኔ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ፖሊሲ ግልጽ መሆኑን ተገንዝቧል። ነገር ግን በዚህ ጉዳይ የውሳኔ ሂደት ላይ፣ ቦርዱ ሜታ የትጥቅ ግጭት ሁኔታዎች ውስጥ የግጭት እና ማነቃቂያ ፖሊሲን እንዴት እንደሚተገብር፣ ለየት ያሉ የፖሊሲ ሁኔታዎች እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ወይም ኩባንያው በልዩ ሁኔታ የሚጠቀምባቸው የማስፈጸሚያ ሂደቶች በተመለከተ በቂ መረጃ አለመሰጠቱን ተገንዝቧል።

*II. ቅቡልነት*

ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ የሚደረጉ ገደቦች ቅቡልነት ሊኖራቸው ይገባል፣ ይህም የሰዎችን መብት ማክበር፣ የሀገር ደህንነትን ወይም የህዝብን ሰላም መጠበቅን ይጨምራል። የግጭት እና ማነሳሳት የሚመለከተው የፌስቡክ የማህበረሰብ ደንብ ከፌስቡክ ይዘት ጋር የሚዛመድ በተጨባጭ የሚፈፀም ጉዳትን ለመከላከል ያለመ ነው። ቀደም ሲል ቦርዱ «በራያ ቆቦ ተፈጽመዋል የሚባሉ ወንጀሎች» በተባለው ውሣኔ ላይ እንደገለጸው፣ በዚህ ፖሊሲ ላይ የተመለከቱ ገደቦች የህይወት እና የአካል ደህንነት መብቶችን የማስጠበቅ ዓላማ አላቸዉ።

### III. *አስፈላጊነት እና ተመጣጣኝነት*

የአስፈላጊነት እና ተመጣጣኝነት መርሆች ሜታ በንግግሮች ላይ የሚጥለዉ ገደብ የጥቃት ስጋትን ለመቀነስ አስፈላጊ መሆኑን እንዲያሳይ ይጠይቃሉ። ገደቦቹም ሰዎችን ከጥቃት ስጋት ለመጠበቅ እና እና ከመጠን በላይ ያልሰፉ መሆን አለባቸዉ (አጠቃላይ አስተያየት 34፣ አንቀፅ 34)። ቦርዱ ይህንን ዉሳኔ በመስጠት ሂደት ላይ፣ ሃገረ-መንግስታት በዓለም አቀፍ ህግ መሠረት ያለባቸዉ ግዴታ እና የንግድ ተቋማት ላይ የሚጣለዉ የሰብአዊ መብት ኃላፊነት ልዩነት ሳይዘነጋ፣ በራባት የድርጊት መርሃ ግብር አንድ ንግግር ግጭት ማነሳሳት ነው ለመባል መሟላት ያለባቸዉን ሁኔታዎች ከግምት አስገብቷል ([ራባት የድርጊት መርሃ ግብር፣ OHCHR፣ A/HRC/22/17/Add.4፣ 2013](#))።

በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ቦርዱ ይህንን ይዘት ከመድረክ ላይ ማስወገድ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ መሰረት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ አስፈላጊ እና ተመጣጣኝ ገደብ እንደሆነ ተገንዝቧል። በራባት የድርጊት መርሃ ግብር ባለ ስድስት ክፍል መመዘኛን በመጠቀም፣ ቦርዱ ይህንን ልጥፍ ለማስወገድ ድጋፍ ያገኛል።

በኢትዮጵያው ያለው ሁኔታ፣ የተናጋሪው ደረጃ እና አላማ፣ የንግግሩን ይዘት እና ተደራሽነት፣ እንዲሁም ጉዳት የመከሰት ዕድል በተጨባጭ ለሚያጋጥም ከፍተኛ ግጭት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። (1) ዐውድ፦ ይዘቱ የተለጠፈው ቀጣይነት ባለው እና እየተባባሰ በመጣ የእርስ በርስ ጦርነት ዐውድ ውስጥ ነው። ግጭቱ ገና ከጅምሩ በሁሉም የግጭት አካላት የተፈጸሙ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊነት መብት ጥሰቶች ተስተውለውበታል። (2) ተናጋሪ፦ ተናጋሪው ትግራይ ታጣቂ ሃይሎችን የመምራት ስልጣንን ጨምሮ ከግጭቱ ውስጥ ከፍተኛ ተፅእኖ ካላቸው አንዱ አካል ጋር ቁርኝነት ያለው የክልል መንግስት ቢሮ ነው። (3) ዓላማ፦ ከቋንቋው እና ከይዘቱ አንጻር፣ ቢያንስ እጃቸውን ያልሰጡ ወታደሮችን ለመግደል ጥሪ እንደተካተተበት እና ተጨማሪ ጉዳት ለማድረስ ዓላማ እንዳለ በምክኒያታዊ ግምት መዉሰድ ይቻላል። (4) ይዘት፦ ልጥፉ በጦርነቱ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ከግምት ሳያስገባ ወታደሮችን እና የፖለቲካ መሪዎችን ኢላማ ማድረግን የሚያበረታታ ነው ተብሎ ሊነበብ ይችላል። (5) የስርጭቱ መጠን፦ ይዘቱ ወደ 260,000 የሚጠጉ ተከታዮች ካሉት የግጭቱ አካል ጋር የተገናኘ ቢሮ ይፋዊ ገጽ ላይ ተለጠፈ ሲሆን ከመወገዱ በፊት ለሁለት ቀናት በመድረኩ ላይ ቆይቷል። (6) የመሆን ዕድል እና ቅርበት፦ ይዘቱ የተለጠፈው የህወሓት ሃይሎች ከትግራይ አልፈው ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች እየገሰገሱ በነበረበት ወቅት እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ ሰላማዊ ዜጎች መሳሪያ እንዲያነሱና እንዲዋጉ ጥሪ ባቀረቡበት ወቅት ነው።

ቦርዱ በዚህ ዉሳኔ ላይ የተመለከተዉን ይዘት ማስወገድ አስፈላጊ እና ተመጣጣኝ መሆኑን ከመገዘብ በተጨማሪ፣ ጉዳዩን ለሚመረምረው ቦርድ ግልጽ የሆነው፣ ሜታ በግጭት እና በተለያዩ የትጥቅ ግጭቶች አውድ ውስጥ የሚወስዳቸዉን እርምጃዎች ተመጣጣኝነት እና ተመሳሳይነት ለመገምገም የበለጠ ግልፅነት እንደሚያስፈልግ ነው። ኩባንያው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ መድረኮቹ የጥላቻ ንግግሮችን ለማሰራጨት እና የብሄር ግጭቶችን ለማባባስ ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሆነ

ያዉቃል። በአንዳንድ ግጭቶች ውስጥ ሜታ የይዘት ግምገማን ለማሻሻል አዎንታዊ እርምጃዎችን ቢወስድም (ለምሳሌ በቦርዱ ምክረ-ሃሳብ መሰረት በእስራኤል እና ፍልስጤም ግጭት ውስጥ በይዘት ግምገማ ሂደት ዉስጥ ያለውን አድሎአዊነት በተመለከተ ገለልተኛ ጥናት ማሰራቱ)፣ ያሉትን ፖሊሲዎች እና ሂደቶችን ለመገምገም እና በግጭት አካባቢዎች ውስጥ ያለውን የይዘት ቁጥጥር መርህ ላይ ያተኮረ እና ግልጽነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ ስራ አልሰራም። አንዳንድ የቦርድ አባላት በግጭት ቀጠናዎች ውስጥ ያለው የሜታ የይዘት ግምግማ በአለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ መሠረት መቃኘት እንዳለባቸዉም አመልክተዋል ።

ሜታ በኢትዮጵያ ዉስጥ ሌሎችን ለግጭት የሚያነሳሳ ይዘትን ለማስወገድ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ዘርዝሯል። ኩባንያው ለአደጋ የተጋለጡ ወይም ግጭት ላጋጠማቸው ሀገሮች ሁለት ጠቅላላ ሂደቶችን ጠቅሷል፣ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የዋሉት፡- «ለአደጋ የተጋለጡ ሀገሮች» የደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት እና IPOC ናቸው። ኢትዮጵያ ከ2020 መገባደጃ ጀምሮ ይዘቱ በተለጠፈበት ጊዜ የደረጃ አንድ ስጋት ላይ ያለች ሀገር (ከፍተኛ ስጋት) ሆና የተመደበች ሲሆን፣ በIPOC ደግሞ ደረጃ ሶስት (ከፍተኛው የስጋት ደረጃ) ተሰጥቷል። ይዘቱ የጣሰው ግልጽ ፖሊሲ መስመር ቢኖርም ይዘቱ ከመድረኩ የተወገደው ከሁለት ቀናት በኋላ ነበር። ከላይ የተገለጸው የራባት መስፈርት ከግምት ሲገባ፣ በትጥቅ ግጭት አውድ ውስጥ ሁለት ቀናት ብዙ መሆኑን ቦርዱ ይገነዘባል። ይህ የሚያሳየው ከፍ ያሉ የሰብአዊ መብት ጥሰት አደጋዎችን የሚያስከትሉ ክስተቶችን ለመቋቋም፣ ለአደጋ የተጋለጡ ሀገራት የሚለዉ የምደባ አሰጣጥ ስርዓት እና IPOC በቂ አለመሆናቸውን ነው።

ሜታ «ለአደጋ የተጋለጡ ሀገሮች» ምደባ የሚሰጥበትን መስፈርት እና በዚህ ምደባ ምክንያት ኩባንያዉ በኢትዮጵያ እና በሌሎች የግጭት ቀጠናዎች ያወጣዉ የወጪ መጠን ላይ በቂ መረጃ ለህዝብ አይሰጥም። ያለዚህ መረጃ፣ ቦርዱም ሆነ ህዝቡ የእነዚህን ሂደቶች ውጤታማነት እና ፍትሃዊነት መገምገም አይችሉም፣ የኩባንያው የሥራ ወጪዎች ፍትሃዊ መሆናቸውን ወይም በሌላ አከባቢዎች ወይም በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ በተመሳሳይ ፍጥነት እና ትጋት መተግበራቸውን መገምገም አይችሉም።

እንደ ሜታ አገላለፅ IPOC «የአጭር ጊዜ መፍትሄ» እና በሚያስፈልግ ጊዜ ብቻ የሚሰበሰቡ ናቸው። ይህ ለቦርዱ የሚያመለክተው ኩባንያው በአጠቃላይ ግጭቱ ለሚወስደዉ ጊዜ ይዘትን በብቃት ለመገምገም እና ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ የሆነውን እውቀት፣ አቅም እና ቅንጅት የሚያቀርብ ዘላቂ የውስጥ አሰራር ከፍተኛ ወጪ በማውጣት መገንባት እንዳለበት ነው። ይህም በተገቢው ፖሊሲ እና ከሚመለከታቸዉ ሀገራት በተዉጣጡ ባለሙያዎች ሊቀረፅ ይገባል።

አሁን በተግባር ላይ ያለዉ ሜታ በግጭት አካባቢዎች ውስጥ የሚከተለዉ የይዘት ግምገማ ወጥነት የጎደለው ዉጤት ሊያመጣ ይችላል። እንደ የውጭ ግንኙነት ምክር ቤት ከሆነ በአሁን ወቅት በዓለም ላይ ወደ 27 የሚጠጉ የትጥቅ ግጭቶች አሉ። በአንዳንድ ታዛቢዎች አተያይ፣ ሜታ ፣ በሌሎች የግጭት ሁኔታዎች ምላሽ ለመስጠት በጣም ረጅም ጊዜ ቢፈጅበትም ቢያንስ በአንድ ግጭት ላይ (ሩሲያ-ዩክሬን) ግን በፍጥነት እርምጃ ወስዷል እንዲሁም በግጭት ማነሳሳት ፖሊሲ

የተከለከሉ ይዘቶችን ለመፍቀድ የሚያስችሉ ልዩ ፖሊሲዎችን መፍጠር ችሏል። በBI የኖርዌይ የንግድ ት/ቤት ተባባሪ ፕሮፌሰር በሆኑት ዶ/ር ሳምሶን ኢሳያስ የተሰጠ አንድ <u>አስተያየት</u> (PC-10433)፣ ሜታ በሩሲያ-ዩክሬን ግጭት አውድ ውስጥ ይዘትን ከመገምገም አንጻር የወሰዳቸው «ፈጣን እርምጃዎች» የተመለከተ ሲሆን፣ «በዚህ ግጭት እና በሌሎች አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች በተለይም በኢትዮጵያ እና በማይናማር ግጭቶች መካከል የተለያያ ሂደቶችን ተከትሏል»። ይህ ወጥነት የጎደለው አካሄድን መኖሩን ያሳያል፣ ይህም በተለይ በትጥቅ ግጭት አውድ ውስጥ የሜታ ተደራሽነት እና አቅም ላይ ችግር ይኖረዋል።

## 9. የቁጥጥር ቦርድ ውሳኔ

የቁጥጥር ቦርዱ የግጭት እና ማነሳሳት የማህበረሰብ ደንብን በመጣሱ ይዘቱ ከመድረክ እንዲወገድ ሜታ ያስተላለፈውን ውሳኔ አጽንቷል።

## 10. የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ

<u>ግልጽነት</u>

1. ቦርዱ «በቀድሞው የፕሬዚዳንት ትራምፕ እገዳ» ወሰኔ ላይ እና በድጋሚ «ሱዳን ሰቅጣጭ ቪዲዮ» ላይ ባቀረበዉ ምክረ ሃሳብ መሰረት፣ ሜታ ስለ ቀዉስ ፖሊሲ ፕሮቶኮሉ መረጃ በበይነ መረቡ ላይ ማቅረብ አለበት። ቦርዱ ይህ ዉሳኔ ከታተመበት በስድስት ወር ዉስጥ ሜታ በግልጽነት ማዕከሉ ላይ ከህዝብ ፖሊሲ ፎረም አጭር ገለፃ በተጨማሪ ራሱን የቻለ ፖሊሲ ሆኖ ስለ ቀዉስ ፖሊሲ ፕሮቶኮሉ መረጃ ሲያሳትም ይህ ምክረ-ሀሳብ ተፈጻሚ እንደሆነ ይቆጥራል።

<u>አፈጻጸም</u>

2. ሜታ በትጥቅ ግጭቶች ጊዜ የይዘት ፖሊሲዎቹን አፈፃፀም ለማሻሻል፣ በብቃት ለመገምገም እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልገውን እውቀት፣ አቅም እና ቅንጅት የሚያቀርብ ዘላቂ የውስጥ አሰራር ዘዴ መመስረት ያለውን አዋጭነት ማጥናት አለበት። ሜታ ለቦርዱ ቀጣይነት ያለው የውስጥ አሰራር አዋጭነት ላይ አጠቃላይ እይታ ሲሰጥ ቦርዱ ይህን ምክረ ሃሳብ ተፈጻሚ እንደሆነ ይቆጥራል።

### * የሂደት ማስታወሻ፦

የቁጥጥር ቦርዱ ውሳኔዎች አምስት አባላት ባሉት ፓናል የተዘጋጀ ሲሆን በአብላጫ ድምፅ ይጸድቃል። የቦርድ ውሳኔዎች የግድ የሁሉንም አባላት ግላዊ አመለካከት አይወክሉም።

ለዚህ ውሳኔ ግብዓት፣ በጎተንበርግ ዩኒቨርሲቲ ዋና መቀመጫዉን ያደረገ እራሱን የቻለ የምርምር ተቋም ለቦርዱ ገለልተኛ ጥናት አቅርቧል። የጥናት ተቋሙ ከስድስት አህጉራት የተዉጣጡ ከ50 በላይ የማህበረሰብ ጥናት ባለሙያዎችን እና ከ3,200 በላይ ከተለያዩ ሀገራት የተዉጣጡ ባለሙያዎችን

ያካተተ ቡድን ነው። ቦርዱ በጂኦፖለቲካዎች፣ እምነት እና ደህንነት እና ቴክኖሎጂ መስተጋብር ዙሪያ አተኩሮ ከሚሰራ ዱኮ አማካሪዎች (Duco Advisors) የተባለ አማካሪ ድርጅት ጭምር እገዛ አግኝቷል።